ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማህበር (ቅሰአድድማ)
Kinijit North America Association of Support Organizations (KNAASO)
766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 www.kinijitna.org Email: kinijitna@kinijitna.org

# የጋራ መግለጫ

ሃገራችን ኢትዮጵያ በወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ትገኛለች ሲባል ላንዳንዶች እንደ ክሊሼ ይታያቸው ይሆናል። ይሁን እንጅ በማንኛውም ታሪካዊ፤ ማህበራዊ፤ ኤኮኖሚያዊ፤ ጂኦ ፖለቲካዊና ተፈጥሮ ሃብታዊ ቀመር ብንለካው በርግጥም ሃገራችን እጅግ በሳሳ ሚዛን ላይ የተንጠለጠለች መሆኗን እንገነዘባለን። ይህ ታዲያ ራሳችንን ለማታለል ፈቃደኛ ካልሆንን ነው።

በ1997 ዓ/ም ምርጫ መዳረሻ ላይ የተካሄዱት አገር አቀፍ ውይይቶች እነዚህን አሳሳቢ ጉዳዮች ቁልጭ አድርገው ለማሳየት በመቻላቸው ብሔራዊ መግባባት ተገኝቶ እንደነበርም መካድ አይቻልም። በዚህም ምክንያት ነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታይቶ በማይታወቅ ስሜት መፍትሔያችን ይህ ብቻ ነው ብሎ በዲሞክራሲ፤ በፍቅር፤ በሠላምና በአንድነት ጎዳና ለመራመድ የቆረጠው። በሺታውን ለይቶ ማወቁ የህክምናው አጋማሽ መሆኑን ስለተረዳ ነበር ብሩህ ተስፋን አሻግሮ ማየት የጀመረው።

በዚህ አንጻር ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ያደረጉት አስተዋጽኦ የሚመሰገን ሆኖ እያለ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የነበረው ድርሻ የላቀ ነበር ብንል ከአድልኦ አይቆጠርብንም። ቅንጅት በሕዝቡ ምናብ ውስጥ ሰርጾ የገባው መነሻየም መድረሻየም ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ አሠራሮች ናቸው ብሎ ስላወጀና በተግባርም ስላሳዬ ነበር። የቅንጅት መሪዎች በገጽታቸውም በሚናገሩትም ቃል ያንጸባረቁ የነበረው ፍጹም ሃቀኝነትን፤ ግልጽነትን፤ ከአፍቅሮተ ራስ የጸዳ የአገርና የሕዝብ መውደድን ስለነበር በሚሊዮን የሚቆጠር ሠራዊትና አድናቂ ሊያፈሩ ቻሉ።

የቅንጅት መስህቦች እነዚህና እነዚህ ብቻ ናቸው። እነዚህ ክቡር እሴቶች በሌሉበት፤ በተበረዙበትና በተመረዙበት ሁኔታ ቅንጅትንና ደጋፊዎቹን የሚያስተሳስረው የወርቅ ሰንሰለት ሊኖር አይችልም።

ለዚህም ነው ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የድጋፍ ድርጅቶች መሪዎቻችንን ለማስፈታትና የዲሞክራሲ ትግሉ እንዳይቀለበስ ሌት ከቀን ከምናደርገው መባዘን ጎን አሠራራችንን ፍጹም ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ የሞት የሽረት ትግል ስናካሂድ የቆየነው። ቅንጅት የሃያአንደኛው ክፍለ ዘመን ፓርቲ እንዳይሆን፤ ቅንጅት ለኢትዮጵያ ህዝብ ቃል የገባበትን ግልጽነትና ተጠያቂነት ያማከለ ዲሞክራሲዊ አሠራር በራሱ ድርጅት ውስጥ እንዳያሰፍን የሚፈልጉ የፈላጭ ቆራጭ ሥርአት አጋፋሪዎች ትግላችን እመርታ ሊያሳይ በሚቃረብበት ወቅት ሁሉ በመንገዳችን ላይ መሰናክል በመጣል ግስጋሴያችንን ሊያዳክሙ ይሞክራሉ። እነዚህ ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሥመር እንዲመጡ ያሳየነውን ትዕግሥትና ያደረግነውን ሙከራ እንደ የዋህነት ስለቆጠሩት ከንግዲህ ለነርሱና የነርሱን ስርዎ መንግሥት ለማስንበት ለሚሯሯጡ ተላላኪዎች የምንቾረው ምንዳ አይኖረንም።

መሪዎቻችን ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራርን የፈጠሩት የሚገኙበትን የማያፈናፍን የእስር ቤት ሁኔታ ካገናዘቡና በርግጥም ተገቢውን አመራር ለመስጠት እንደማይችሉ ከተረዱ በኋላ ለመሆኑ የሚያነጋግር እንኳ አይደለም። የሰጡት የሥልጣን ውክልና የመልካም ማኔጅመንትን ወግ

የተከተለ ነበር። "ከውጭ መንግሥታትና ከኢሕአዴግ ጋር ከሚደረጉ ድርድሮች/ስምምነቶች በስተቀር" የፓርቲውን ሥራ በውክልና እንዲያካሂድ ዓለም አቀፍ አመራሩን መሥርተዋል። እንኳንስ የሞት ፍርድን ያህል ዳመና በላዩ የሚያንዣብብበት የህሊና እስረኛ ይቅርና የዓመት ፈቃድ የሚወስድ ሃላፊ እንኳ ውክልና ሲሰጥ ለትንሹም ለትልቁም ጉዳይ እየደወላችሁ ፈቃዴን አግኙ አይልም።

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር አባላት በክፍለ ዓለማችን እየተካሄደ ያለውን ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ቅንጅት ሴራ ቴሌኮንፈራንሶች አካሂደው ከመረመሩ በኋላ፤

1. ለዓለም አቀፍ አመራሩ ስድስት ሰዎች በቂ ናቸው ብሎ የወሰነው የቅንጅት አመራር ሌላ ስድስት ሰዎችን እንዲያክል ከተደረገም በኋላ ከቅንጅት መወለድ ጋር ከስሞ የነበረውን የቡድን ስሜት በሚያስቀድሙ ግለሰቦች ተንኮል ቤቱ የውዝግብ ቤት ሆኖ የትግሉን ግስጋሴ እንዳስናከለው በመገንዘብ፤
2. እነርሱን እስካመቻቸው ድረስ ቅንጅት ዓለም ዓቀፍ አመራርን እናውቃለን የሚሉ፤ ካላመቻቸው ደግሞ አናውቅም እያሉ ሕብረተሰቡን ሲያሳዝኑ የቆዩ ግለሰቦች ከቃሊቲ በመጣ መመሪያ መሠረት ዓለም አቀፍ አመራሩን እንደገና አውቀውና አምነው ሰኔ 2 ቀን 1999 ዓ/ም ሰነድ ፈርመዋል። የዚህ ሰነድ መፈረም በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የእፎይታ እስትንፋስ እንዳመጣ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ይሁን እንጅ ይህ ውል የተፈረመበት ቀለም ሳይደርቅ ቀደም ሲል የመጣውን የመሪዎች መመሪያ የሚጻረርና መሪዎቻችንን የማይሽት ሌላ መመሪያ መጥቷል በማለት አዲስ የውዥንብር ፕሮፓጋንዳ ከፍተዋል። ስለሆነም፤ ይህ የትግል ፈር የሚያስት ዘመቻ የተጀመረው በመሪዎቻችን ላይ እስከ ሞት የሚደርስ ብይን በተሰጠበትና ትግላችንን ከምንጊዜም በበለጠ ማስተባበር በሚገባን ማግስት መሆኑን በመረዳት፤
3. መሪዎቻችን በእስር ባሉበት ሁኔታ በቂ መረጃ የማግኘት ዕድል ስለሌላቸው የፖለቲካ አቅጣጫዎችን ለመመዘንና በአግባቡም አመራር ለመስጠት እንደማይችሉ አከራካሪ አይሆንም። የሚደርሳቸውን የተበጣጠሰና አንዳንዴም ሆን ብሎ የተዛባ መረጃ ሃቀኛነት ለማመሳከር በሚችሉበት ዓለም ውስጥም አይኖሩም። ስለሆነም፤ ይህን የመረጃ ክፍተትና ቀዳዳ በመጠቀም የግልና የቡድን ጥቅማቸውን ለማራመድ የሚሯሯጡ ቡድኖች መሪዎቹን ለማሳሳት ተደጋጋሚ ሙከራ እያደረጉ መሆናቸውን በመገንዘብ፤
4. በመግቢያችን ላይ ያቀረብነውን ያገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በማድረግ፤ ህዝባችን ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነት በማገናዘብ፤ ቅንጅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል ኪዳን የገባበትን ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ዲሞክራሲያዊ ያሠራር ባህል በራሱ ድርጅት ውስጥ የማዳበር ሃላፊነት እንዳለበት በመገንዘብ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፈናል፤

(ሀ) 12 አባላት የሚገኙበት ዓለም አቀፍ አመራር እርቅ መስርቶ ሃገር በማዳን ተግባር ላይ እንዲሰማራ ከመሪዎቹ የተሰጠውን መመሪያ የተቀበልነው በታላቅ ደስታ ነው።

(ለ) ዓለም አቀፍ አመራሩ ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ መሠረት ስምምነት ፈርሞ መልካም እንቅስቃሴ በጀመረበት ሰዓት በይዘትም ሆነ በቅርጽ ዲሞክራሲያዊ ባህርይ የሌለው፤ ካለፈው መመሪያ ጋር የሚቃረን፤ ፕሮፌሽናሊዝም የጎደለውና የከረመ ሌላ ደብዳቤ ከሸማግሌ ተብየዎቹ ኪስ ብቅ ማለቱ አፍራሽ ተልዕኮ ያለው ሆኖ ስላገኘነው ፈጽሞ አንቀበለውም።

(ሐ) ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር በመሪዎቻችን አስተዋይ ውሳኔ የተፈጠረ ጊዜያዊ መዋቅር መሆኑን በመገንዘብ ከምስረታው ጀምሮ ያላቋረጠ ድጋፍ ስንሰጥ ቆይተናል። አስራ ሁለቱ አባላት ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን መሠረት አድርገው እስከሠሩ ድረስ

ያልተቆጠበ ድጋፋችንን እንደሚያገኙ እናረጋግጥላቸዋለን። ከዚህ ጋር በማያይዝ ቅንጅት በውጭው ዓለም የሚያገኘው ድጋፍና የሚቀዳጀው ድል አባሎቻችን ቀን ከሌት በሚያደርጉት መስዋዕትነት እንጅ ከሕዝብ ጋር ግንኙነት የሌላቸው መዋቅሮች ስለተፈጠሩ እንዳልሆነ ግንዛቤ እንዲኖር እንፈልጋለን።

(መ) ለቅንጅት ያለን ድጋፍ የሚመነጨው በማኒፌስቶው ላይ በግልጽ ከሰፈሩት እሴቶች ስለሆነ ለተግባራዊነታቸው በቆራጥነት እንታገላለን። ይህ ደግሞ ዲሞክራሲን በመሻት ክቡር ሕይወታቸውን መስዋዕት ያደርጉ ወገኖቻችን፤ የሞቀና የደመቀ ቤታቸውን ትተው በእስር የሚማቀቁ መሪዎቻችን፤ እንዲሁም የ 77 ሚሊዮን ሕዝብ አደራ ስለሆነ ለድርድር እንኳ የምናቀርበው አይደለም።

ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት የሚከበርባት ኢትዮጵያ እውን ትሆናለች!

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
ሰኔ 10 ቀን 2007 ዓ/ም

<u>ግልባጭ፤</u>
ለቅንጅት አመራር አባላት - ቃሊቲ
ለቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር አባላት - በያሉበት
ለቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች - መላው ዓለም